የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ

አጭር ማብራሪያ

መግቢያ

ሀገራችን ኢትዮጵያ በበርካታ ለውጦች ውስጥ እያለፈች ሲሆን፣ ለውጡ ዲሞክራሲን፣ ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት እንዲሁም እድገት እና ልማት ለማረጋገጥ የሚያስችል የፖለቲካ ስርዓት ሊያረጋግጥ የሚችል መሆኑ በብዙዎች ዘንድ ተስፋ ቢደረገም በለውጡ ደስተኛ ያልሆኑና የተለያዩ ፍላጎቶች ያላቸው የውስጥና የውጪ ሀይሎች ለውጡን ለመቀልበስ በቅንጅት በርካታ አፍራሽ ተልእኮዎችን እየፈፀሙ ይገኛሉ፡፡ ሌላው ለውጡን እየፈተነው የሚገኘው በሃገሪቱ ልሂቃን መካከል በተለያዩ መሰርታዊ ጉዳዮች በተለይም በሀገራዊ መግባባት እጅግ በሚያስፈልግባቸው ጭብጦች ዙርያ ያለው ተቃርኖ ነው። ይህ እጅግ መሰረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሳይቀር የሚስተዋለው ሰፊ የሆነ የሀሳብ ልዩነትና አለመግባባት የተረጋጋ እና የሰከነ ዲሞክራሲያዊ ስርዐት መገንባትን እጅግ አስቸጋሪ የሚያደርገው በመሆኑ መፍትሄ የሚሻ ጉዳይ ነው። በልሂቃን መካከል በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ መግባባት አለመኖሩ፣ በመካከላቸው ያለው አለመተማመን እና ጥርጣሬ የዲሞክራሲ ሽግግር ሂደቱን እጅግ ፈታኝ አድርጎታል። ይህ ቅራኔ እና መዘዙ ከልሂቃን አልፎ በማህበረሰቡ ውስጥ እየሰረፀ ከፍተኛ ምስቅልቅል ማስከተሉ እሙን ነው።

ሀገራት እንዲህ አይነት ፈተና ሲያጋጥማቸው ሀገራዊ መግባባት ለማምጣት የተለያዩ ዘዴዎችን የሚጠቀሙ ሲሆን ከነዚህ ዘዴዎች መካከል አንዱና በአሁኑ ወቅት በብዙ ሀገሮች ተሞክሮ ውጤታማ እየሆነ የመጣው ሀገራዊ ውይይት ነው፡፡ በመሆኑም በሀገራችን እየተስተዋሉ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት ሀገራዊ ውይይት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ የታመነበት ሲሆን፣ ይህን ሀገራዊ ምክክር የሚመራ እና የሚያሳልጥ አካል በህግ ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ አዋጅ የተዘጋጀ ሲሆን የአዋጁ ማብራሪያ በሚከተለው መልኩ ቀርቧል፡፡

የአዋጁ አስፈላጊነት

በሀገራችን በተለይም በፖለቲካ ልሂቃኑ መካከል በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ እየተፈጠረና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን ልዩነት መፍታት ለሀገራዊ አንድነት መሰረታዊ ነገር ነው፡፡ እንዲህ አይነት ሁኔታዎች በኢትዮጵያ ብቻ የተፈጠሩ ሳይሆኑ በሽግግር ላይ በነበሩ በርካታ ሀገራት ያጋጠሙ ችግሮች ናቸው፡፡ እንዲህ አይነት ፈተናዎችን አልፈው ስኬታማ የዲሞክራሲያዊ ሽግግር ያደረጉ ሃገራት ተሞክሮ እንደሚያሳየው አካታች ሃገራዊ ምክክሮችን ማድረግ መሰረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተሻለ መግባባት እንዲኖር እና በሂደትም የመተማመን እና በወሳኝ ሃገራዊ ጉዳዮች ላይ ተቀራርቦ የመስራት ባህልን ለማጎልበት ጠቃሚ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። አካታች ሃገራዊ ውይይቶች በሀገራዊ ፖለቲካ ቀውስ ወቅት ፣ ከጦርነት በኋላ ባሉ ሁኔታዎችና፣ መጠነ ሰፊ የፖለቲካ ሽግግሮች በሚደረግበት ጊዜ፣ በብዙ ባለ ድርሻ አካላት መካከል መግባባትንና ለችግሮች ዘላቂ መፍትሄ ለመፍጠር ያለሙ መድረኮች ሲሆኑ እነዚህ መድረኮች በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ሃገራዊ መግባባት ለመፍጠር ተመራጭ ናቸው፡፡

በመሆኑም ሀገራዊ ምክክሮችን አካታች በሆነ መንገድ ማካሄድ የሀገራችንን ችግሮች በመፍታት ዘላቂ ሰላም እንዲሁም ጠንካራና ቅቡልነት ያለው ሀገረ መንግስት ለመገንባት ያስችላል፡፡ እንዲሁም ሰላም የሰፈነባት፣ እየዳበረ የሚሄድ፣ ዲሞክራሲያዊ ስርዐት ባለቤት የሆነች፣ ዘላቂ እና ፍትሃዊ እድገት የሚመዘገብባት ኢትዮጵያን የማየት ተስፋን እውን ለማድረግ መደላደል የሚሆን ሃገራዊ መግባባት መሰረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ለመፍጠር እና ለማጎልበት ሀገራዊ ውይይት አስፈላጊ ነው። ሃገራዊ መግባባት ሊኖርባቸው በሚገቡ ጉዳዮች ላይ አካታች የሆነ የምክክር እና የውይይት ሂደት ሰፊ መሰረት ያለው ስምምነት፣ መግባባት እና የጋራ አቋም እንዲኖር ለማድረግ ያስችላል ። በተቻለ መጠን መሰረታዊ የሚባሉ ሃገራዊ ጉዳዮች በተለያየ ጎራ የተሰለፉ የፖለቲካ ልሂቃንም ሆነ ምልዐተ ህዝቡ ተቀራራቢ እና ለሃገራዊ አንድነት ገንቢ የሆነ አቋም እንዲይዙ ማድረግ የአካታች ሃገራዊ ምክክሩ ዋነኛ ግብ ነው።

ሃገራዊ ውይይቶች ወጤታማ እና ሰፊ ተቀባይነት ያላቸው እንዲሆኑ ግልፅ የሆነ መዋቅር ሊኖራቸው ይገባል። የሂደቱ ተዓማኒነት በዋናነት ምክክሩን እንዲያሳልጥ እና እንዲመራ ወይም እንዲያካሂድ በሚሰየመው አካል ብቃት እና ገለልተኝነት ላይ ይወሰናል። ይህን ሀገራዊ ምክክርን የሚያስተባብርና የሚመራ አካል በአብዛኞቹ ዜጎች ዘንድ ተዐማኒ የሆነ እና ቅቡልነት ያለው፣ ግልጽ የሆነ የጥቅም ግጭት የሚያመጣ የፖለቲካ ዝንባሌ ወይም ግብ የሌለውና በአብዛኛው የምክክሩ ተሳታፊዎች ዘንድ በገለልተኛነቱ የታመነበት መሆን ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም የዚህ አዋጅ አላማ ይህን ስራ የሚመራና የሚያስተባብር ተቋም ማቋቋምና ስራውን የሚመሩና የሚያስተባብሩ አካላት የሚመረጡበትን ግልፅ ስርአት መዘርጋት ነው፡፡

የአዋጁ አደረጃጀት

አዋጁ በመግቢያ፣ በአምስት ክፍሎችና በሰላሳ አንቀፆች የተደራጀ ነው፡፡ በክፍል አንድ ስር ጠቅላላ ድንጋጌዎች ማለትም አጭር ርዕስ፣ ትርጓሜንና አገራዊ ምክክሩ የሚመራባቸው መርሆዎችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ይዟል፡፡ ክፍል ሁለት ስለኮሚሽኑ መቋቋም፣ ዓላማ፣ አደረጃጀት እና ተግባርና ኃላፊነቶችን የሚመለከቱ በተለይም ስለ መቋቋም፣ ስለ ዋና መስሪያ ቤት፣ ስለ ኮሚሽኑ ዓላማ፣ የኮሚሽኑን አደረጃጀትና የስራ ዘመን፣ የኮሚሽኑ ተግባርና ኃላፊነቶችና ስለ ኮሚሽኑ ስብሰባ ስርአት ተደንግጓል፡፡ በክፍል ሶስት ኮሚሽነሮችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ተካተውበታል፣ በተለይም ስለኮሚሽነሮች ቁጥር፤ ስለኮሚሽነሮች አሰያየም ለኮሚሽነርነት ስለሚያበቁ መስፈርቶች፣ የኮሚሽነሮች ደመወዝና ጥቅማጥቅም፣ የኮሚሽነሮች ሙበትና ግዴታ፤ ኮሚሽነሮች ከኃላፊነት ስለሚነሱበት ሁኔታ፣ ኃላፊነትን በገዛ ፍቃድ ስለመልቀቅና ኮሚሽነርን ስለመተካት የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ተደንግገዋል፡፡ በክፍል አራት ስለኮሚሽኑ ምክር ቤት፣ ዋና ኮሚሽነር፣ ምክትል ዋና ኮሞሽነር እና ፅህፈት ቤት በተለይም ስለኮሚሽኑ ምክር ቤት ተግባር እና ስልጣን፣ የኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር እና ምክትል ዋና ኮሚሽነር ተግባር እና ስልጣን፣ ሰለኮሚሽኑ ጽህፈት ቤት፣ የኮሚሽኑ ጽህፈት ቤት ተግባር እና ሥልጣን እና የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ተግባር እና ስልጣንን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ተካተዋል፡፡ በክፍል አምስት ውስጥ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ማለትም ስለ ኮሚሽኑ የበጀት ምንጭ፣ ስለሂሳብ መዛግብት፣ ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን፣ ተፈፃሚነተ ስለማይኖራቸው ህጎችና አዋጁ የሚፀናበት ጊዜን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ይገኙበታል፡፡

የአዋጁ ይዘት

የአዋጁ ስያሜ *“የኢትዮጵያ ፌዴራዊ ምክክር ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ”* የሚል ሲሆን ከሚቋቋመው ተቋም ተልዕኮ ጋር የሚጣጣም ስያሜ ለመስጠት ተሞክሯል። በመግቢያው የተለያዩ የፖለቲካ እና የሃሳብ መሪዎች እንዲሁም የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል እጅግ መሠረታዊ በሆኑ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ሰፊ የሆነ የሃሳብ ልዩነት፣ አለመግባባት እና ተቃርኖ የሚታይ በመሆኑ፤ ይህን አለመግባባት እና ተቃርኖ ለማርገብ እና ለመፍታት ሰፋፊ አገራዊ የሕዝብ ምክክሮችን አካታች በሆነ መንገድ በማካሄድ አገራዊ መግባባት መፍጠር አስፈላጊ መሆኑ ተመላክቶዋል። እነዚህ ሀገራዊ ምክክሮች ተቀባይነት እና ተዐማኒነት ያላቸው እንዲሆኑ ምክክሮቹን የሚያመቻቹውና የሚመራው አካል ብቃትና እና ገለልተኝነት ወሳኝ መሆኑን ፤ የምክክር ሂደቱን በብቃትና በገለልተኝነት ለመምራትና ለማስተባበር የሚችል ተቋም ለማቋቋም ይህን አዋጅ ማውጣት አስፈላጊ መሆኑ ተገልጿል፡፡

በትርጓሜ ስር በአዋጁ ላይ በስራ ላይ የዋሉትንና ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ቃላትና ሀረጋት ተተርጉመዋል፡፡ የኮሚሽኑን መቋቋም የሚደነግገው አንቀፅ ስር ከፖለቲካ፣ ከማንኛውም የመንግስት ወይም ሌላ አካል ተጽእኖ ነጻ የሆነ የሚል ሀረግ እንዲገባ የተደረገ ሲሆን የዚህ ሀረግ መግባት አስፈላጊነት ኮሚሽኑ በተቻለ መጠን ከየትኛውም ተፅእኖ ነፃ እንዲሆን ለማድረግ ሲሆን ይህንኑ ለማጠናከር የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሆን ተደርጓል፡፡

የኮሚሽኑ ዓላማ በአዋጁ አንቀጽ 6 ስር የተገለፀ ሲሆን ምክንያቱም የኮሚሽኑ ተልእኮ እና ግብ ምን እንደሆነ ምንም አይነት ብዥታ ሳይኖር ወደ ስራ መግባት እንዲችል ለማድረግ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የኮሚሽኑ ዓላማዎች በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል መሰረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ለተፈጠሩ ልዩነቶች መሰረታዊ ምክንያቶችን መለየት፣ ውይይቶቹ የሚካሄዱባቸውን ርእሰ ጉዳዮች በመለየት ውይይት እንዲደረግባቸው ማመቻቸት፤ የሚካሄዱት ሀገራዊ ውይይቶች አካታች፣ ብቃት ባለውና ገለልተኛ በሆነ አካል የሚመራ፣ የአለመግባባት መንስኤዎችን በትክክል በሚዳሰስ አጀንዳ የሚመራ፣ ግልጽ በሆነ የአሰራር ስርአት የሚመራ እና የውይይቱን ውጤቶችም ለማስፈጸም የሚያስችል እቅድ ያለው እንዲሆነ በማድረግ ውጤታማ የሆኑ ሀገራዊ ውይይቶችን ማካሄድ፤ የሚካሄዱት ሀገራዊ ውይይቶች በተለያዩ የፖለቲካ ልሂቃን፣ በመንግስት እና በህዝብ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሻሻል፣ መተማመን የሰፈነበትና አዲስ የፖለቲካ ስርዓት ለመፍጠር በሚያስችል አግባብ ውይይቶቹ እንዲካሄዱ ስርአት መዘርጋት፣ ከውይይቶቹ የተገኙ የመፍትሄ ሀሳቦችን በስራ ላይ እንዲውሉ ድጋፍ በማድረግ በፖለቲካ ልሂቃን፣ በህዝቦች፣ በመንግስትና በህዝቦች መካከል መተማመን የሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ ስርአት በሀገር አቀፍ ደረጃ መገንባት መሆናቸውን ተመልክቷል፡፡

የኮሚሽኑን አደረጃጀት በተመለከተ የኮሚሽኑ ምክር ቤት ፤ ዋና ኮሚሽነር፤ምክትል ዋና ኮሚሽነር፤ ጽህፈት ቤት፤አስፈላጊ ኮሚቴዎች እና አስፈላጊ ሰራተኞች እንደሚኖሩት የተደነገገ ሲሆን ኮሚሽኑ እነዚህ አካላት ካሉት ስራውን በአግባቡ መወጣት ያስችለዋል የሚል እምነት በመኖሩ እነዚህ አደረጃጀቶች እንዲኖሩት ተደርጓል፡፡

የኮሚሽነሮችን አሿሿም በተመለከተ አንቀፅ 11 እና 12 ስር የተቀመጠ ሲሆን ፤ የጠቅላይ ሚኒስትር ፅሕፈት ቤት ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ኮሚሽነር ሊሆኑ የሚችሉ ግለሰቦችን ጥቆማ በኋላ ኮሚሽነር ሊሆኑ የሚችሉ አስራ አራት ዕጩዎችን አንቀፅ 13 ስር በተቀመጠው መስፈርት መሠረት በመለየት የዕጩዎቹን ዝርዝር ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፡፡ ይህም ዕጩ የማቅረብ ሂደቱን ግልፅና ተዓማኒ እንዲሆን ይረዳዋል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩም የዕጩዎች ዝርዝር ከቀረበለት በኋላ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየት አስራ አንድ ዕጩዎችን የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስቀርቦ እንዲሾሙ ያደርጋል።

የኮሚሽኑ የስራ ዘመን 3 ዓመት ሲሆን፣ ነገር ግን ስራው በሶስት አመት ውስጥ ካልተጠናቀቀ የኮሚሽኑ የስራ ዘመን በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሊራዘም እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ የኮሚሽኑ ተግባርና ኃላፊነቶች በተመለከተም ተወያዮችንና የውይይት አጀንዳዎችን ከመምረጥ ጀምሮ በውይይቶቹ የሚገኙ ምክረ ሀሳቦችን በተግባር ላይ ለማዋል የሚያስችል ግልፅ እና ተጨባጭ የሆነ እቅድ መዘጋጀቱን አስከማረጋገጥና አስፈላጊውን እገዛ እስከማድረግ የሚደርስ ተግባርና ሀላፊነቶች ተሰጥተውታል፡፡

የኮሚሽነሮች ቁጥር አስራ አንደ (11) እንዲሆኑ የተደረገ ሲሆን፣ ኮሚሽኑ የኮሚሽነሮችና የሰራተኞች ቁጥር ሳይንዛዛ የተወሰኑ ኮሚሽነሮችንና ባለሙያዎችን ይዞ ውጤታማ ስራ እንዲሰራ ታስቦ ነው ቁጥራቸው እንዲያንስ የተደረገው፡፡ የኮሚሽነሮች አሰያየምን በተመለከተ በህዝብ፣ በፖለቲካ ድርጅቶች እና በሲቪል ማህበራት እንዲጠቆሙና በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሾሙ የተደረገ ሲሆን ይህም ነፃና ገለልተኝነታቸውን ለማረጋገጥ ከሚያስችሉ መንገዶች አንዱ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ እንዲሁም ለኮሚሽነርነት የሚያበቁ መስፈርቶች ተብለው የተቀመጡትኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው፤ ሁሉንም ሀይማኖቶች፣ የተለያዩ ብሄሮች ብሄረሰቦችንና ህዝቦችን በእኩል አይን የሚያይ፣ የማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ አባል ያልሆነ፤ ሀገራዊ መግባባት እንዲኖር ተግቶ የሚሰራ፤መልካም ስነ-ምግባርና ስብዕና ያለው፤በህዝብ ዘንድ አመኔታ ያለው፣ በከባድ ወንጀሎች ተከሶ የጥፋተኝነት ውሳኔ ያልተላለፈበት፣ የኮሚሽኑን ስራ በአግባቡ ለመስራት የሚያስችል የተሟላ ጤንነት ያለው፤ እና ሙሉ ጊዜውን ለኮሚሽኑ ስራ ለማዋል ፍቃደኛ የሆነ በሚል የተዘረዘሩ ሲሆን እነዚህን መስፈርቶች የኮሚሽነሮች አባላት በተቻለ መጠን ገለልተኛና ለሁሉም አካል እኩል እይታ እና ሁለንም አካል እኩል ያገለግላሉ የሚል እምነት ለማሳደር የሚያበቁ በመሆናቸው ነው፡፡

ስለ ኮሚሽኑ ምክር ቤት፣ የኮሚሽኑ ምክር ቤት ተግባር እና ስልጣን፣ የኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር እና ምክትል ዋና ኮሚሽነር ተግባር እና ስልጣን እንዲሁም ስለኮሚሽኑ ጽህፈት ቤት እና ስለፅህፈት ቤቱ ሀላፊ ስልጣንና ተግባራት በዝርዝር ለማስቀመጥ ተሞክራል፡፡

ተጨማሪ ማብራሪያ የሚሹ ጉዳዮች[1]

- **አጀንዳዎች እና ተሳታፊዎች እንዴት ለምን በአዋጁ አልተገለፁም? ምክክር የሚደረግባቸው አጀንዳዎች የትኞቹ ናቸው?**

ምክክር ሊደረግባቸው የሚገቡ ርዕሰ ጉዳዮችን፣ እንዲሁም በሂደቱ ተሳታፊ የሚሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ተለይተው በአዋጁ እንዲደነገጉ አልተደረገም። ይህ ያልተደረገው፣ የምክክር እና የውይይት አጀንዳዎችን እንዲሁም ተሳታፊዎችን ግልፅ፣ አሳታፊ እና አሳማኝ በሆነ መንገድ ሃገራዊ ምክክሩን ለማሳለጥ የሚቋቋመው ኮሚሽን መለየት እንዲችል እድል ለመስጠት ነው። ገለልተኛ እና ብቃት ያላቸው ኮሚሽነሮች የህዝብን ፍላጎት፣ የሃገሪትዋን ነባራዊ ሁኔታ እና ታሪክ ከግምት በማስገባት

[1] በረቂቅ አዋጁ ላይ ከዚህ ቀደም ከፖለቲካ ፓርቲዎች እና ከሲቪል ማህበረሰብ ተወካዮች ጋር በነበሩ የውይይት መድረኮች ከተነሱ ጥያቄዎች እና ርዕሰ ጉዳዮች መካከል በአንፃራዊነት የተዴጋገሙ እና ተጨማሪ ማብራሪያ የሚሹ ናቸው ተብለው የታመኑ ጉዳዮች በዚህ ይማብራሪያው ክፍል በአጭሩ ተዳሰዋል።

አግባብነት ያላቸውን ሳይንሳዊ መንገዶች በመጠቀም ሃገራዊ ፋይዳ ያላቸውን እና እጅግ መሰረታዊ ከመሆናቸው የተነሳ ሃገራዊ መግባባት ሊኖርባቸው የሚገቡ ጭብጦችን በተሻለ ሁኔታ ሊለዩ ይቻላሉ። ይህን ለማድረግ እንዲችሉ እድል ለመስጠት ሲባል አዋጁ ውስጥ ዝርዝር የምክክር አጀንዳዎችን መደንገግ አልተፈለገም። የምክክር ሂደቱን ተሳታፊዎችም በተመለከተ፣ በየተኛው ደረጃ፣ በምን አይነት አካሄድ እና መስፈርት ተሳታፊዎች እንደሚመለመሉ የአሰራር ስርዐቱ በአዋጅ በዝርዝር ከሚቀመጥ ይልቅ ለኮሚሽኑ ቢተው የተሻለ ነው የሚል አቋም ተወስዶዋል። ገለልተኛ እና ብቁ የሆኑ ኮሚሽነሮች ይህን አሰራር ቢዘረጉ እና ዝርዝር ጉዳዮችን በመመሪያ ቢወስኑ ይበልጥ ውጤታማ የሆነ ስራ ለመስራት ይችላሉ ተብሎ ታምኖዋል። ረቂቅ አዋጁ ኮሚሽኑ ስራውን የሚሰራበትን ጠቅለል ያለ ተቋማዊ እና ሕጋዊ ማዕቀፍ እንዲይዝ የተፈለገ ሲሆን ከዚህ አልፎ ዝርዝር አሰራሮችን እና የፍሬ ነገር ጉዳዮችን ያካተተ ከሆነ ኮሚሽነሮቹ ሃገራዊ ምክክር ሂደቱን ለመንደፍ እና ለማሳለጥ የሚኖራቸውን ነፃነት እና እድል ያሳጣል የሚል ስጋት አለ። ሆኖም ለኮሚሽኑ የሚሰጠው ይህ ነፃነት በአዋጁ ውስጥ በተካተቱት እና ሂደቱን ሊገዙ ይገባል በተባሉት መርህዎች እና ሌሎች ድንጋጌዎች ማዕቀፍ ውስጥ ያለ ስለሆነ ገደብ የለሽ ነፃነት አይደለም።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው ነገር ሃገራዊ ፋይዳ ያላቸው እጅግ ብዙ ርዕሰ ጉዳዮች ያሉ በመሆኑ ፣ እነዚህን ሁሉ ጉዳዮች አሳታፊ በሆነ የምክክር ሂደት ለመዳሰስ ቢሞከር መቋጫ እና ብዙም ፍሬ የሌለው እና እጅግ የተንዛዛ ሂደት ውስጥ የመግባቱ አደጋ ነው። በዚህ ረገድ ሊሰመርበት የሚገባው ነገር፣ ሃገራዊ የምክክር ኮሚሽን እየተቋቋመ ያለው ምክክር ቢደረግባቸው ጠቃሚ የሆኑ እና ሃገራዊ ፋይዳ ያላቸው ጉዳዮች ሁሉ ላይ ውይይት ለማካሄድ አይደለም። በየተኛውም ማህበረሰብ ውስጥ፣ በተለይም በዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ውስጥ የሃሳብ ልዩነት ተፈጥሮአዊ እና ጤናማ ነው። ሃገራዊ በሆኑ የተለያዩ የፖሊሲ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የፖለቲካ መሪዎች እና ደጋፊዎቻቸው የሃሳብ ልዩነት ይኖራቸዋል። እንደዚህ ያሉ የሃሳብ ልዩነቶች በዲሞክራሲያዊ ሂደት በሚኖር ፉክክር እና ትብብር ከርክር እየተደረገባቸው፣ በምርጫ እየተለዩ የመንግስት ፖሊሲ እየሆኑ ይተገበራሉ ወይም በተፎካካሪዎች የሚቀርብ የፖሊሲ አማራጭ ሆነው እየተፈራረቁ ይቀጥላሉ። በዚህ አይነት መንገድ የሚስተናገዱ የፖሊሲ ልዩነቶች የዲሞክራሲያዊ ስርዐት ባህሪያዊ መገለጫ ናቸው። ሆኖም የሃገረ መንግስትን ህልውና የሚፈታተኑ፣ ዲሞክራሲያዊ አብሮነትን አዳጋች የሚያደርጉ በመሰርታዊ ጉዳዮች ላይ የሚፀባረቁ ተቃርኖዎች ከፖሊሲ አማራጮች በተለየ መንገድ ሊታዩ ይገባል። የሃገረ መንግስቱን ቅቡልና በከፍተኛ ሁኔታ የሚገዳደሩ ተቃርኖዎች እልባት አግኝተው፣ ሃገራዊ መግባባት በመሰረታዊ ሃገራዊ ጉዳዮች ላይ በብዙሃኑ ዘንድ ካልኖረ የሃገር ህልውናን ማረጋገጥም ሆነ ዲሞክራሲያዊ ስርዐት መገንባት አይቻልም። ስለዚህ ሃገራዊ ምክክር ሊያተኩርባቸው የሚገባው እና ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባው ሃገራዊ መግባባት ሊኖርባቸው የሚገባ፣ የሃገረ መንግስቱን ህልውና እና ቅቡልና ለማጠናከር ወሳኝ ሚና ያላቸው አንኳር ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ነው።

- **ምክክር ስንል ምን ማለታችን ነው?**

በዚህ አዋጅ አውድ “ምክክር” ሲባል ምን ማለት ነው? ምክክር ከውይይት፣ ምክክር ከድርድር በምን ይለያል የሚሉ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ። ብዙ ጊዜ ውይይት የሚለውን ቃል ስንጠቀም፣ ሃሳብ መለዋወጥ እና ማንሸራሸር ላይ ያተኮረ መስተጋብር ሲሆን ምክክር ደግሞ የሃሳብ ልውውጡ የጋራ መፍትሄ ፍለጋ ላይ ያተኮረ እንደሆነ የሚያመላክት በመሆኑ ከ“ውይይት” ይልቅ “ምክክር” የሚለው ቃል ተመራጭ ሆኖዋል። ኢትዮጵያውያን በሃገራዊ ምክክር ሂደቱ የጋራ በሆኑ ጉዳዮች ላይ፣ የጋራ መፍትሄ ፈልገን፣ በመፍትሄዎቹ ላይ በመግባባት ሃገራዊ አንድነት እና ህብረታችን ማጠናከር ይገባናል በሚል መነሻ የተዘጋጀ አዋጅ ስለሆነ “ምክክር” የሚለው አገላለፅ ይበልጥ ተገቢ ነው። እውቀት መገብየትን ወይም ግንዛቤ

ማግኘትን በራሱ የመጨረሻ ግብ ያደረገ ውይይት ሳይሆን በዋነኝነት መፍትሄ እና ምክረ ሃሳብ የሚገኝበት ሂደት ለማካሄድ ታስቦዋል። እንዲሁም ሂደቱ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ወገኖች ጥቅም እና አቋማቸውን ታሳቢ አድርገው፣ በመስጠት እና መቀበል እይታ የሚያካሂዱት ድርድር ሳይሆን፣ ልሂቃንንም፣ አብዛኛውንም ማህበረሰብ ባካተተ መንገድ የጋራ መፍትሄ የሚፈለግበት አካሄድ ስለሆነ "ድርድር" የሚለው አገላለፅ ተመራጭ አይደለም። ሆኖም የምክክሩ ሂደት በውስጡ ውይይት እና ድርድርንም ያካተተ አውድ ሊኖረው ይችላል። ምክንያቱም ውይይት፣ ድርድር እና ምክክር የሚወራረስ ገፃታ ሊኖራቸው ስለሚችል ነው።

- **ከሂደቱ የሚጠበቀው ተጨባጭ ውጤት ምንድን ነው?**

በሃገራዊ ምክክር ሂደቱ የሚጠበቀው ዋናው ነገር ሃገራዊ መግባባትን ለማምጣት፣ የሃገረ መንግስቱን ቅቡልና ለማሳደግ የሚረዱ ግልፅ እና ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ምክረሃሳቦች ናቸው። ምክረሃሳቦቹ በሚደረገው ሃገራዊ ውይይት እና ምክክር ሂደት የመነጩ፣ የአብዛኛው ዜጋ ድጋፍ ያላቸው፣ ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉ እና ሃገራዊ አውዱን ከግምት ያስገቡ እንደሚሆኑ ይጠበቃል። ምክረ ሃሳቦች ኮሚሽነሮቹ እንዲሁ በዘፈቀደ ወይም በግላቸው በጎ መስሎ የሚታያቸውን ሃሳብ ሳይሆን አካታች በሆነ እና ሰፊ ሃገራዊ የምክክር ሂደት፣ መግባባት እየተፈጠረባቸው እና እየበሰሉ የሚመጡ የመፍትሄ ሃሳቦች መሆን አለባቸው። በመጨረሻው የሚመጡት ምክረሃሳቦች ዋጋ፣ ጥቅም እና ተቀባይነት በሃሳቦች ይዘት ላይ ብቻ ሳይሆን ሃሳቦቹ በመነጩበት ሂደት ጥራት ላይም የተመረኮዘ ነው። ስለዚህ የሂደቱ ግልፅነት፣ አሳታፊነት እና ተዐማኒነት ወሳኝ ነው። እንዲህ ባለ ሂደት የመነጩ እና ተቀባይነት ያላቸው ምክረ ሃሳቦች ተግባራዊ ሲደረጉ ሃገራዊ መግባባትን ያጠናክራሉ። ምክረሃሳቦቹ እንዳግባብነቱ በፌደራልም ሆነ በክልል መንግስታት ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ አካላት የሚፈፀሙ ሊሆኑ ይችላሉ።

- **የኮሚሽኑ ገለልተኝነት እንዴት ይረጋገጣል ?**

የኮሚሽኑን ገልተኝነት ለማረጋገጥ በረቂቅ አዋጁ የተለያዩ ድንጋጌዎች ተካተዋል። በቅድሚያ ኮሚሽነሮች የሚሾሙበት ሂደት ለህዝብ ግልፅ እና የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ሲቪል ማህበረሰቡን እና ሌሎች የማህብረሰብ ክፍሎችን የሚያሳተፍ እንዲሆን ጥረት ተደርጎዋል። በተጨማሪም ኮሚሽነሮች ከፓርቲ ፖለቲካ ገለልተኛ የሆኑ እንዲሆን አስገዳጅ ድንጋጌ ተካቶዋል። እንዲሁም ኮሚሽነሮች ከሃላፊነት ሊነሱ የሚችሉበትን መንገድ ጠበቅ ያለ እና ነፃነታቸውን የሚያስጠብቅ እንዲሆን ተደርጎዋል። ኮሚሽነሮች በወንጀል ያለመከሰስ ከለላ እንዲኖራቸውም ተደርጎዋል። እነዚህ ድንጋጌዎች የኮሚሽነሮችን ገለልተኝነት ለመጠበቅ ከፍተኛ አስትዋፅዖ ይኖራቸዋል ተብሎ ይጠበቃል።

ማጠቃለያ

በሀገራችን በመሰረታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የሚስተዋሉትን ልዩነቶች ሃገራዊ ምክክር ጉባኤ በማካሄድ ወደ ሀገራዊ መግባባት ማምጣት የሚያስፈልግ ሲሆን፣ ይህን ሂደት ውጤታማ የሚያደርጉ ሁሉም ባለድርሻ አካላትም እንዲሳተፉ መደረግ አለበት፡ : መድረኩን የተለያዩ እና ብዙ ተዋንያንን በማቀላጠፍና በመምራት እንዲሁም በማገዝ የሚያሳትፉ ቢሆንም በተቻለ መጠን ገለልተኛ ሆኖ እነዚህን አካላት የሚመራና የሚያስተባብር አካል ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ ኮሚሽኑ እንዲቋቋም ተደርጓል፡

፡ በመሆኑም ሁሉም ሀገር ወዳድ ዜጋና ትውልደ ኢትዮጵያዊ የኮሚሽኑ ስራ ውጤታማ እንዲሆን ሚችለውን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡